**የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት**
**WOLKAIT-TEGEDE-SETIT-HUMERA HUMAN RIGHTS ORGANIZATION**
**P.O.Box 132414 Columbus, OH 43213; E-mail: Wolkait.Tegede@yahoo.com**

**ኮሎምበስ ኦሃዮ መስከረም 18 ቀን 2002 ዓ/ም የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጆች ስብሰባ ላይ ስለ ወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት እንቅስቃሴ**
**የቀረበ አጭር ዘገባ (ሪፖርት)፤**

ክቡራትና ክቡራን የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ተወላጆች፤

በዛሬው ቀን እዚህ በመገኘት ስለ ወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት ዓላማና እንቅስቃሴ ለእናንተ ለጉዳዩ ባለቤቶች ሪፖርት ለማቅረብ ዕድሉን ስላገኘን በድርጅቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የወልቃይት ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ በየትኛውም አካባቢ እንደሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቱ የተከበረና ተፈጥሮ የለገሰውን እውቀትና ሐብት በተገቢ መጠቀም ያልቻለ፣ እንደቀረው ሕዝብ መብቱን ለማስከበር የታገለ፣ የአገሩን ዳር ድንበር ከባዕዳን ሲከላከልና ሥፍር ቁጥር በሌላቸው ልጆቹ ክቡር መስዋዕትነት አስከብሮ የቆየ፣ ከቀረው ኢትዮጵያዊ ለየት ባለ መልኩ የደስታውንም ሆነ የሐዘን ስሜቱን፣ በትግርኛም በአማርኛም ሲገልፅ የኖረ፣ የተሻለ ሕይዎት ፍለጋ ከየትኛውም የአገሪቱ አካባቢዎች (ከኤርትራ ጭምር) የሚመጡ ወገኖቹን አድልዖ ሳያደርግ ያስተናገደ፣ የተዋለደና አብሮ የኖረ ኩሩ ሕዝብ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ይኽ ኩሩና ታታሪ ሕዝብ ዘመናዊ የእርሻ ልማት በማስፋፋት ከቀረው አካባቢ ኢትዮጵያዊ ይበልጥ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የደረሰና ጅምሩ በደርግ መምጣት ባይደናቀፍ ኖሮ የልማቱ ሥራ ለአካባቢው ብቻ ሣይሆን ለአገሪቱ ብልፅግናና የኤኮኖሚ እድገት ምን ያኽል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችል እንደነበር በኩራትና በፀፀት መናገር ይቻላል፡፡

ይህ ሕዝብ የንጉሡን አገዛዝ ከሥልጣን መወገድ ተከትሎ በተደረገው ትግልም በተለይ በኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ- ኢዲዩ) ዓርማ ሥር የታገለና ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለ ጀግና ሕዝብ ነው፡፡ የአካባቢው ተወላጆች በኢድኅ ብቻ ሣይሆን በኢሕአፓና በኋላም በከፋኝ ድርጅት እንደታገሉ ይታወቃል፡፡ በተደረገው ፀረ-ደርግ መራር ትግልም ብዙዎች የአካባቢው ተወላጅ የሆን በወያኔ (ሕወሓት) ድርጅት ውስጥ ገብተን እስከ መጨረሻው ታግለናል፣ መስዋዕትነት ከፍለናል፣ ለደርግ መውደቅም ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገናል፡፡

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ በማንነቱ፣ በኢትዮጵያዊ ጠንካራ እምነቱና በታጋይነቱ ምክንያት በደርግ ተደጋጋሚ ዘመቻና ደርግ ከተወገደ በኋላም የተረፈ ንብረቱ እንዲወድም፣ ሰብዓዊ መብቱ እንዲረገጥና በራሱ መሬት ላይ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ እንዲታይ፣ ሰላማዊ ኑሮው እንዲመሰቃቀል፣ በርካታ ልጆቹን እንዲያጣ፣ ብዙዎችም ለስደት ተዳርገው በሱዳን ስደተኛ ሠፈሮችና በዓለም ዙሪያ እንዲበተኑ ተደርጓል፡፡

የወልቃይት ሕዝብ ባለው ለየት ያለ ባህል ምክንያት ኢትዮጵያዊነቱን እንጂ የጠበበ የጎሣ ፍረጃ ውስጥ እራሱን ያላስገባ ሕዝብ በመሆኑ ማንኛውንም ሰው የሚለካው በምግባሩ እንጂ በሚናገረው ቋንቋ አልነበረም፡፡ ያም በመሆኑ የአካባቢው ተወላጅ ሁሉ ማንኛውንም ሰው

በሚናገረው ቋንቋ ምክንያት አድልዖ ሳያደርግና ቋንቋን ሕዝብ የመለያ ምክንያት አድርጎ ሳያይ የኖረ ሕዝብ መሆኑ ይታወቃል::

ሆኖም ግን ደርግ ከመውደቁ በፊት ጀምሮ በወያነ ሐርነት ሕዝብ ትግራይ ቁጥጥር ሥር የወደቀው ይህ ሕዝብ ከታሪካዊ ማንነቱ አንፃር ዘፈኑም ሆነ ልቅሶው በጥቅሉ ሁለንተናዊ ባህሉን በአማርኛ የሚያንፀባርቅ መሆኑ እየታወቀ በዚህ የእሱነቱ ብቻ በሆነ ያሸበረቀ ባህሉና ማንነቱ ምክንያት ፍዳውን እንዲያይና በታሪኩ አይቶት በማያውቅ መልክ አቤቱታውን ሁሉ በትግርኛ ቋንቋ ብቻ እንዲያቀርብ፣ እጅግ ብዙ ሥመ-ጥር የሆኑና የተከበሩ የራሱ ጀግኖች እንደሌሉት ሁሉ ትምሕርት ቤቶችና ተቋሞች በትግራይ ተወላጆች ስም እንዲሰየሙ የሆነበት፣ ምን ዓይነት ዘፈን እንደሚዘፍን ሣይቀር ቁጥጥር የተደረገበትና በሁለተኛ ዜጋነት የሚያስፈርጅ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ እንዲገኝ ተደርጓል::
ይህ ደግሞ በተለይ የደርግን አረመኔ አገዛዝ ለማስወገድና አገራችን ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የሰፈነባትና የዜጎች እኩልነት የተረጋገጠባት እንድትሆን በማሰብና በማመን በዚህ ድርጅት ሥር ለታገልን የአካባቢው ተወላጆች እጅግ አሳዛኝና ልንቀበለው የማንችል ጉዳይ መሆኑ ግልፅ ነው:: የትግራይ ወገናችንን ጨምሮ የቀረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እኩልነቱ እንዲረጋገጥና ዴሞክራሲያዊ መብቱ እንዲከበርለት ይህን ድርጅት አምነንና ተቀብለን የታገልንና መስዋዕትነት የከፈልን የአካባቢው ተወላጆች እንዴትስ የራሣችን ወላጆችና የሥጋ ዘመዶች በቀን ተቀን ኑሯቸው ሣይቀር እንደሁለተኛ ዜጋ ሲታዩ፣ አኩሪ ታሪካቸው ተፍቆ አዲስ የፈጠራ ታሪክ ሲሰጣቸውና አልፎም የበይ ተመልካችና ተፈናቃይ ሲደረጉ ስናይና ስንረዳ ምን ያኽል ኅሊናን የሚበጠብጥ፣ ግራ የሚያጋባና ለማመን የሚያስቸግር እንደሆነ መገመት ይቻላል:: ብዙዎቻችን ሁኔታው ተቀባይነት የሌለውና ከአግባብ ውጭ በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥም ሆነ በኢሕአዴግ አማካይነት እንዲስተካከል ብዙ ሙከራዎች አድርገናል::
በስደት ዓለም ያለው የአካባቢው ተወላጅ ወገናችንም ሁኔታውን ለመለወጥና የሕዝቡን መብት ለማስከበር በልዩ ልዩ ደረጃና መንገድ ጥረት አድርጓል::

የአካባቢያችን ሕዝብ የሚደርስበትን ግፍና በደል ለማስቀም፣ ሰብዓዊ መብቱንና ክብሩን ለማስጠበቅ በግለሰብ ደረጃ ጀምሮ በተሰባሰበ መልክ የነበረውን ጥረት የበለጠ ውጤት ሊያመጣ በሚችል መንገድ ሰፋ ባለ መልኩ ተደራጅቶ መንቀሳቀሱ አስፈላጊና የተሻለ በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህንን "የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት" በመማቋቋም እነሆ ትግላችንን በሰላማዊ መንገድ ቀጥለናል::

ክቡራትና ክቡራን፤

የድርጅታችን ዓላማ፣ የእንቅስቃሴአችን ስልት፣ ያደረግናቸው ጥረቶች፣ ወደፊት ማከናወን ያሰብናቸው የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችንና የገጠሙንና ወደፊትም የሚገጥሙንን ችግሮችና መሰናክሎች በአጭር በአጭሩ አቀርባለሁ::

<u>ዓላማችን:-</u> ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ በአጭሩ እንደተገለፀው ሁሉ የአካባቢው ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን የሰብዓዊ መብት መጣስ፣ አጠቃላይ መፈናቀልና ፈርጀ ብዙ ተደራራቢ ግፍና በደል ለማስቀም፣ ታሪካዊ ማንነቱ ታውቆ የውስጥ አስተዳደሩንም ሆነ የልማት እንቅስቃሴውን እራሱ በፈለገውና በፈቀደው መልክ እንዲመራ ለማስቻል የአካባቢውን ተወላጆች በያሉበት አደራጅቶ የተቀናጀ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ነው::

<u>የእንቅስቃሴአችን ስልት:-</u> ድርጅታችን ስሙ እንደሚያመለክተው የሰብዓዊ መብት ድርጅት ነው:: ዓላማውና ተልእኮውም የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራን ሕዝብ ሰብዓዊ መብት ለማስጠበቅ ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ እየሠራ ባለው ሕገ-መንግሥት መሠረት የሕዝባችን መብት እንዲከበርና ለችግሩ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መፍትኄ እንዲገኝ ከተራ አቤቱታ ጀምሮ በልዩ ልዩ ደረጃና መንገድ ለማዕከላዊ መንግሥትም ሆነ ለክልሉ መንግሥት ማሳሰብና መጠየቅ የመጀመሪያው እርምጃችን ነበር::

ለማእከላዊ (ፌዴራላዊ) መንግሥትም ሆነ ለክልሉ መንግሥት የምናቀርበው አቤቱታ፣ ጥያቄና ማሳሰቢያ ሁሉ የአገሪቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ልዩ ልዩ የመንግሥት ተቋማት፣ በውጭም በውስጥም ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብና አልፎም የዓለም ኅብረተሰብ እንዲያውቁት፣ ከሕዝባችን ጎን እንዲቆሙና ትግላችንን እንዲደግፉ ለማድረግ ተሞክሯል። ይኸንን የሰብዓዊ መብትና ክብር ዘመቻችንን ያደረግነውና የምናደርገው ሙሉ በሙሉ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው።

ያደረግናቸው ጥረቶች፡- በሕዝባችን ላይ የተፈፀመውንና እየተፈፀመ ያለውን ግፍና በደል ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሳወቅና መፍትሔ ለማስገኘት በብዙ ወገኖቻችን በልዩ ልዩ ጊዜዎችና መንገዶች ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል። ድርጅታችን የተቋቋመውም እነዚህ ጥረቶች የተሻለ እንዲጎለብቱና ሰላማዊ ትግሉ ተጠናክሮ አስቸኳይ መፍትሔ ለማስገኘት ከማሰብ እንጂ ሁላችንንም ለሚያዳክም የእርስ በርስ ፉክክር ውስጥ ለመግባት አይደለም። እንደዚያ ዓይነት አጉል ፉክክር ወይም ሽሚያ ውጤቱ ጊዜንና አቅምን መበተን፣ ትግላችንን ማዳከምና በሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን ጭቆንና ግፍ ማራዘም ብቻ ስለሚሆን ከእኛም ሆነ ከማንም ቅን አሳቢና ለሕዝብ መብት ተቆርቋሪ የሚጠበቅ አይደለም።

በዚህ አጋጣሚ ከዚህ ቀደም የሕዝባችንን ብሶት፣ በደልና የሚደርስበትን መከራ ለማስቆም የኢትዮጵያ ሕዝብና የዓለም ኅብረተሰብ እንዲያውቅ በልዩ ልዩ መንገድ የሞከሩ የአካባቢው ተወላጆችን በድርጅታችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ። አሁንም ይህንን የጋራ ትግል አንድ ላይ ተሰባስበን እንድንቀጥል በትህትና እጠይቃለሁ።

በቅድሚያ ያደረግነው በመጀመሪያው ዙር ለመሰባሰብ ጊዜውና ፈቃደኝነቱ ያላቸውና የሚችሉ የአካባቢው ተወላጆችን ማግኘትና የዚህ ሰላማዊ ትግል ዓላማ ላይ የጠራ ግንዛቤ ኖሮን በተደራጀ መልክ እንዴት መንቀሳቀስ እንደሚቻል መወሰን ነበር። በመቀጠልም በተደራጀ መልክ ሰላማዊና ሕጋዊ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚያስችሉንን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ የድርጅቱን ፕሮግራም፣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና የአባላት ቅጽ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር። እነኝህን እያሟላን ግን የሕዝባችንን አቤቱታ በደብዳቤዎች፣ በተለያዩ የጽሑፍ መግለጫዎችና የራዲዮ መግለጫዎች አማካይነት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የክልል መንግሥት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፣ የመንግሥት ተቋማት፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና የዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብ እንዲያውቁት አድርገናል። ስብሰባዎችንም አድርገናል።

በዚህ ረገድ የእንቅስቃሴአችንን ዓላማ ሕጋዊና ሰላማዊ መሆኑን ግልጽ በማድረግ፣ እራስን በራስ የማስተዳደር ሕገ-መንግሥታዊ መብታችን እንዲረጋገጥ ከሚጠይቅ ጀምሮ *የክልል አንድ (የትግራይ ክልል) የአካባቢውን ተወላጆች በማፈናቀል ከአራት-መቶ ሽህ በላይ የትግራይ ተወላጆችን አስፍሮ፣ የአካባቢው ተወላጆች ሰብአዊና የዜግነት መብቶቻቸው ተገፎ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲቆጠሩና በተራ የጉልበት ሥራ ላይ አገልጋይ እንዲሆኑ፣ ከብቶቹን እንኳ የሚያሰማራበት መሬት አጥቶ እንዲንገላታ፣ እንዲሰቃይና እንዲፈናቀል እየተደረገ መሆኑ አልበቃ ብሎ ሕዝባችንን አጠቃላይ ተፈናቃይ ለማድረግ ባለው ቀጣይ እቅድ መሠረት የሸኽ መሐመድ አላሙዲን ንብረት የሆነ በእርሻ ሥራ ላይ የሚሠማራ የኤኮኖሚ ተቋም በአካባቢው ለማንቀሣቀስ ሥራ መጀመሩን* በተመለከተና በሕዝባችን ላይ በየጊዜው የሚደርሱ ግፎችን እየተከታተልን ለማሳወቅ ሞክረናል። ለክልል አንድ (ትግራይ ክልል) መንግሥት ሕዝባችን የደርሰበትን በደልና ብሶቱን በመዘርዘር በጽሑፍ ገልፀናል፣ ለክልሉ ባለሥልጣኖች አስረድተናል። አጥጋቢ ምላሽ ግን አልተገኘም።

ድርጅቱ የተቻለውን ያህል የአካባቢውን ተወላጆች በተቻለ መጠንና የተቻለውን ያህል ለማሰባሰብ ሙከራዎች አድርጓል፣ አሁንም እያደረግን ነው። ሕዝባችን መብቶቹ እስኪረጋገጡለት ድረስ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ ግፍና መንገላታት ከልብ ያሳሰበውንና የሚቆረቁረውን የአካባቢ ተወላጅ ሁሉ ከማሰባሰብ ወደ ኋላ አንልም።

እቅዳችን፡- ድርጅታችን ሁሉንም ተቆርቋሪ የአካባቢው ተወላጆች አቅፎ ሰላማዊ ትግሉን በተሻለ ተደራጅቶ በልዩ ልዩ ፈርጆች ሚጧጧፍ እንዳለበት ያምናል፡፡ ይህንን እምነቱንም በተግባር ለመተርጎም ከአገር ሽማግሌዎች ጀምሮ ወጣቱ በየአካባቢው እንዲደራጅና ትግሉን በተቀናበረ መልክ እንዲቀጥል ጥረታችን ይቀጥላል፡፡

እስካሁን ላቀረብናቸው አቤቱታዎች በክልሉ መንግሥት በኩል አጥጋቢ ምላሽ አለማግኘታችን ግልጽ ነው፡፡ በኛ በኩል ግን አሁንም ቢሆን የሕዝባችንን ብሶትና ጥያቄ መንግሥትም ይሁን የመንግሥት አካላትና ተቋማት እንዲያውቁት ጉትጎታችንን እንቀጥላለን፡፡
በእርግጥ የእኛ ጥያቄ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ተለይቶ ብቻውን መልስ ላያገኝ ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነፈገውን ዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት በመሬቱ ላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ ቁም ስቅሉን የሚያየው የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ በችሮታ ይሰጠዋል ብለን አናስብም፡፡ ስለሆነም ለአገራችን ሰላም፣ አንድነትና ለሕዝባችን ዴሞክራሲን የሚመኙና ለዚህም የሚታገሉ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችና ወገኖች ሁሉ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራን ሕዝብ ሕጋዊ ጥያቄ ጥያቄአቸው አድርገው ከጎናችን እንዲቆሙ ያስፈልጋል፡፡ ጥሪያችንንም አሁንም በድጋሜ እናቀርባለን፡፡

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ መብት ተረግጦ በየትኛውም አካባቢ ያለ ኢትዮጵያዊ መብቱ ይከበራል ማለት አይቻልም፡፡ በኛ እምነት ወገናችን የትግራይ ሕዝብም ይሁን በሁላችን ትግልና መስዋዕትነት ለሥልጣን የበቃው የሕወሓት ድርጅት አባላት ጭምር የያዝነውን ሰላማዊ የፍትኅና የርትዕ ሕጋዊ ጥያቄ እንዲደግፉና ከጎናችን እንደሚሰለፉ እምነታችን ነው፣ እነሆ ጥሪያችንንም እናቀርባለን፡፡

<u>የገጠሙንና ወደፊትም የሚገጥሙን አንዳንድ ችግሮች፡-</u> ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለፀውን ዓላማቻችንን እውን ለማድረግ የምናካሂደው የሕዝብ መብት የማስከበር ሰላማዊ ትግል የሚጠበቁም ያልተጠበቁም ብዙ እክሎችና እንቅፋቶች ገጥመውታል፡፡

የመጀመሪያው በራሣችን በአካባቢው ተወላጆች ውስጥ የተከሰተው ችግር ነው፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ባለው ችግር ማዘኑ፣ ማሰቡና ሁኔታው እንዲቀየር ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያለው መሆኑ ባያጠራጥርም፣ በአገራችን ውስጥ በተካሄደው የረጅም ጊዜ ትግል ሕዝባችን እንደቀረው አካባቢ የአገራችን ሕዝብ በልዩ ልዩ ድርጅቶችና የትግል ልምዶች ውስጥ ያለፈ ስለሆነ በመካከላችን ሁኔታዎችን በተለይም ችግሮቻችንን የምናይበትና ለማስወገድ መከተል በሚገቡን መንገዶችና ዘዴዎች ላይ የተለያዩ አመለካከቶችና የፖለቲካ እምነቶች መከሰታቸው የሚጠበቅ ነው፡፡

ስለሆነም የጋራ ችግራችን መፍትኄ እንዲያገኝ ሁላችንም በጋራ እንዳንቆም አንዳንድ ችግሮች ተከስተዋል፡፡ ውሎ አድሮ ግን በመኻላችን ውይይት እየተካሄደና እየተመካከርን ልዩነትን እያጠበብን በሂደት ይበልጥ መግባባት እየተፈጠረ ሰላማዊና ትግላችንን ማስተባበርና ማጠናከር እንችላለን የሚል እምነት አለን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሕዝባችንን ጥያቄ አንድ ላይ ቆመን በተጠናከረ መልክ እንዳናቀርብና ሕዝባችን እንዳይተባበር በክልሉ መንግሥት በኩል በመካከላችን ክፍፍል ለመፍጠር የሚደረገው ዘመቻ ነው፡፡ አንዳንዶቹን በልማት ስምና በልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለልና ሌሎቹንም የትግላችንን ትክክለኛ ገፅታ በማዛባት አንዱ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት እንደተነሣን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአካባቢው የሚደረገውን “ልማት” ለማደናቀፍ ሆን ተብሎ የተሸረበ ተንኮል አድርጎ በማቅረብ፣ ሲያሻቸው ደግሞ በአንዳንድ ተቃዋሚ ድርጅቶች የምንገፋና ሕዝባችንን በተለይ ወደ መሣሪያ ትግል እንዲገባ መጠቀሚያ ለማድረግ እንደሆነ፣ አንዳንዴም ግማሹ የነሱ የውስጥ ተላልኪ እንደሆነ አስመስሎ

በማስወራት፣ ምክንያት ሲያጥርባቸው ደግሞ አልፈው ተርፈው አንዳንዶቻችን ጤና ከማጣት የምናደርገው ነገር እንደሆነ በማናፈስ በተወላጁ መኻከል እርስ በርስ መተራጠርና አለመተማመን እንዲሰፍንና አንድነታችን እንዳይጠናከር ለማድረግ ታስበው የተደረጉ መሰሪ ዘመቻዎችን ታዝበናል፡፡ በየጊዜውም ልዩ ልዩ ዘዴዎችን መሞከራቸው አይቀርም፡፡

ቃት ተመድባል የሚባለው መሬት ለወልቃይት ሕዝብ ታስቦ ሣይሆን በአንዳንድ የድርጅቱ (የወያኔ) መሪዎች ዘንድ "ታላቋ ትግራይን" ለመመሥረት ካላቸው ህልምና ለዚህች "ታላቅ ትግራይ" የውጭ መገናኛ በተለይ ከፖርት ሱዳን ጋር የሚያገናኝ ምቹ መተላለፊያ ለመፍጠር እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡ በዚህ ተራ ሽፍጥ ጀግናው የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ ይታለላል ብለው ማሰባቸው እራሱ ሕዝባችን ያለውን ከፍተኛ ኢትዮጵያዊ አገር-ወዳድ ስሜት አለመረዳታቸውንና ምን ድረስ እንደተናቀ ብቻ ነው የሚያሳየው፡፡

ሦስተኛ በአንዳንድ የትግራይ ተወላጅ ወገኖቻችን በተለይም በተቃዋሚው ክፍል አለን በሚሉት ዘንድ ሕጋዊ ጥያቄአችንን ፀረ-ትግራይ እንቅስቃሴ አድርገው ለማየት የሚያደርጉት ሙከራ ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ የድሮ ሕወሓት መሪዎችና ካድሬዎች ድርጅቱ ሲነሣ ይዞት የተነሣው "የትግራይ ሪፑብሊክ" የመመሥረት ዓላማ ከጎንደር ወልቃይትና ጠለምትን ከወሎ ደግሞ "አላ ውሃ ምላሽ" የተባለውን ወደምትገነጠለው ትግራይ የማጠቃለል እምነትን አሁንም ስለሚያቀነቅኑ፣ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ መብቴ ይከበር፣ ታሪኬና እኔነቴ ይታወቅ የሚል ሕጋዊ ጥያቄውን ትግራይን የመጋፋት አድርገው በመቁጠራቸው ሰላማዊ እንቅስቃሴአችንን "የአማራ ሴራ" አድርገው ያዩታል፡፡ የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ መብቴ ይከበር ማለትን በተጣመመ መልክ ተርጉመው አገር እንደመገንጠል ከባድ ወንጀል አድርገው ስለሚቆጥሩት በበጎ አያዩትም፡፡ በመካከላችንም ልዩነት እንዲፈጠር ሙከራዎች ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡ ሆኖም ለነዚህ ወገኖች ግልፅ እንዲሆንላቸው የምንፈልገው በኛ በኩል ያቀረብነው ጥያቄ በራሱ በኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት የተቀመጡ በተለይም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አስመልክቶ የተደነገጉ መተኪያ የሌላቸው የሰው ልጅ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ብቻ እንጂ ሌላ ድብቅ አጀንዳም ሆነ ፀረ-ትግራይ አቋም ያለውም ሆነ ሊኖረው የሚችል እንዳልሆነ እንዲረዱልንና፣ ሲሆን ሁላችንም የአንድ አገር ዜጎች ነንና ለዚህ ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል አብረውን እንዲቆሙ፣ ቢያንስ ግን ተቃውሞአቸውን መለስ ብለው እንዲያስቡበትና እንዲፈትሹት ነው፡፡

በአራተኛ ደረጃ ያለው ችግር ኢሕአዴግን በሚቃወሙ አንዳንድ ድርጅቶችና ቡድኖች የሚደረጉ ሙከራዎች ናቸው፡፡ ይኸም በአብዛኛው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ጠበንጃ ተሸካሚና መሸጋገሪያ እንዲሆናቸው ሰላማዊ ትግላችን ባኅሪውን እንዲቀይር ለማግባባት የሚደረገው እኩይ ተግባር ነው፡፡

የእኛ ትግል ለተወሰነ አካባቢ የአገሪቱ ዜጎች የሚደረግ ውሱንና ሰላማዊና ሰላማዊ ብቻ ነው፡፡ በአገራችን የጦርነት አዙሪት እንዲያከትምም ምኞታችን ነው፡፡ ሆኖም ማንም ሰው ወይም ድርጅት በመረጠውና ያዋጣል በሚለው መንገድ ትግሉን ማድረግ መብቱ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ያ ሲባል ግን ብዙ መከራ ያየ ሕዝባችን ዳግም ባልመከረበትና አስፈላጊነቱን ባልወሰነበት ሁኔታ ሌሎች ወደ ጦርነት እንዲወስዱት ግን አንፈልግም፣ አንፈቅድምም፡፡ ያ ውሳኔ የሕዝቡና የሕዝቡ ብቻ ይሆናል፡፡

ክቡራትና ክቡራን ወገኖቸ፤

በመጨረሻም በወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ተደራራቢ ግፍና መከራ በዚህ ድርጅትና አሁን ባለነው አባላት አቅም ብቻ ሊቆምና የሕዝባችን ሕጋዊ መብቶች ሊከበሩ እንደማይችል ሁላችንም እንድንረዳው እፈልጋለሁ፡፡ ሕዝባችን አሁንም እየተፈናቀለ፣ ቀን በቀን አድልዖ እየተፈፀመበትና ግፍና በደል እየደረሰበት ይገኛል፡፡

የሕዝባችን መሬት በልማት ስም ለውጭ ከበርቴዎች እየተሸጠ በሚገኝበት ምክንያትም ይሁን የአገራችን ሕዝብ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶቹን ለማስከበር በሚያደርገው የተለያየ ትግል፣ ለሱዳን አሣልፎ እየተሰጠ ባለው የድንበር ጉዳይም ይሁን በሚቀጥለው ግንቦት በአገራችን ይደረጋል በሚባለው ምርጫ፣ በመንግሥት በኩል በሚወሰዱ ልዩ ልዩ እርምጃዎችም ይሁን ተቃዋሚው ክፍል በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት፣ ወይም በውስጣችንና በመኻላችን አንድነታችንን በሚፈታተኑ ችግሮች ምክንያት ወደፊት ትግላችን ብዙ ያልተጠበቁ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላል። ስለሆነም ሁላችንም በተለይም ወጣቱ ትውልድ ሁኔታዎችን በቅርበት እየተከታተልንና እየተመካከርን ይህንን ሰላማዊ ትግል እንድናጠናክረውና ለሕዝባችንን እንድንደርስለት በአክብሮት እንጠይቃለን። በርቀት ሣይሆን በቅርብ ሆነን በመመካከር ይህንን ድርጅት ስህተቱን በማረምና ጉድለቱን በማሻሻል ልናጠናክረውና ለውጤት ልናበቃው ይገባል። በኛ በኩል የሕዝባችን ሙሉ መብት እስኪከበር ድረስ ሰላማዊ ትግሉን እንደማናቆም ግልፅ ማድረግ እንፈልጋለን።

በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው አድልዖና በደል ይቁም!
አንድነታችንን እናጠናክር!!
ኢትዮጵያ በአንድነትና በነፃነት ለዘላለም ትኑር!!!

ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

የወልቃይት-ጠገዴ-ሰቲት-ሁመራ የሰብዓዊ መብት ድርጅት ሥራ-አፈጻሚ ኮሚቴ

መስከረም 18 ቀን 2ሽ ሁለት ዓ/ም
(September 28, 2009)